# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
FEDERAL SUPREME COURT

የሰ/መ/ቁ. 239911

ጥቅምት 06 ቀን 2015 ዓ.ም.

ዳኞች፡-

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

**አመልካች፡-** አቶ ጌቱ ስነወልደየስ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ዚነት አብዱ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 02 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 299723 በጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 202286 ሕዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች 1ኛ ተጠሪ ፣ተጠሪ አመልካች እንዲሁም በዚህ ክርክር የሌሉት ወ/ሮ ውብዓለም ጫኔ 2ኛ ተጠሪ ነበሩ፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው አመልካች ታህሳስ 08 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ በነበርንበት ጊዜ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ በቀድሞ አጠራር ቀበሌ 01 ኮኮብ ቁጥር 2 መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የተሰራ ቤት እና በተጠሪ ስም ያለ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-99714 ቶዮታ መኪና ከፍቺ በኃላ ንብረት ሳንከፋፈል ያሸሹት፣ በትዳር ወቅት በተጠሪ ስም በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ግምቱ

ብር 500,000 ብር የሆነ የልብስ መሸጫ ሱቅ የነበረንና ንብረቶቹን ያሸሸች ስለሆነ፣አረብያን መጅሊስ፣ቲቪ 21 ኢንች፣ ፍሪጅ፣አልጋ ከነፍራሹ፣ሙሉ የኪችን እቃዎች በጋራ ያፈራን ስለሆነ እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 28 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጡት መልስ ቤት የተባለው ከጋብቻ በፊት በ1997 ዓ.ም በግሌ የገዛሁት መሰረቱ የወጣ የግሌ ቤት ነው፤ የታርጋ ቁጥር ኮድ 2-99714 የሆነች መኪና አመልካች በማረሚያ ቤት እያሉ በነበረብኝ ወጪ የተሸጠና ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም የዋለ ነው፤ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ግምቱ ብር 500,000 የሆነ ልብስ መሸጫ ሱቅ ንብረትነቱ የግሌ ቢሆንም ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት በኪሳራ የተዘጋ ነው፤ የቤት እቃ አረብያን መጅሊስ የእህቴ ንብረት ሲሆን ሌሎቹ ከአመልካች ጋር ከመጋባታችን በፊት የተፈራ ስለሆነ የጋራ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኃላ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ በኮኮብ ቁጥር 1 የመኖሪያ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ 72 ካ.ሜ ይዞታ ተጠሪ በ1996ዓ.ም በማህበር በመደራጀት ያገኙት እና በማህበሩ ስም ካርታ የተሰጠው በ29/11/97 ዓ.ም እንዲሁም የግንባታ ስምምነት በ17/09/1999 ዓ.ም የተሰጠው መሆኑን፤ በይዞታው ላይ የግንባታው መጠን መሰረቱ የወጣ ዘጠኝ ፋቲንግ ወጥቶ የተቀመጠ ወለል የሌለው ግንባታ መሆኑን የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያስረዱ በመሆኑ እና የግራቀኙ ግንኙነት ከቀን 19/9/1999 ዓ.ም እስከ ግንቦት 26/2005 ዓ.ም ድረስ የቆየ በመሆኑ የተጠቀሰው ቤት ግራቀኙ በጋብቻ እያሉ የተፈራ ስለመሆኑ አያረጋግጥም ፤ የግንባታ ፕላን ስምምነቱ በቀን 17/09/1999 ዓ.ም የተሰጠ መሆኑን ከመግለጹ ውጭ የተጠቀሰው መሰረት የወጣለት ግንባታ በጋብቻ ወቅት የተገነባ ስለመሆኑ አያረጋግጥም ስለሆነም አመልካች ያሉት የተሰራና የሚከራይ ቤት የሌለና በአንጻሩ በይዞታው ላይ መሰረቱ የወጣ ዘጠኝ ፋቲንግ የተቀመጠ ወለል የሌለው ግንባታ መሆኑን የቀረቡት ማስረጃዎች የሚያስረዱ በመሆኑ በጋብቻ ወቅት የተፈራ እንካፈል በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ አደረገው፤ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2-99741 መኪና ግራቀኙ በትዳር እያሉ የተሸጠና ገንዘቡም ለትዳር ጥቅም የዋለ ስለመሆኑ የተጠሪ ምስክሮች በተሻለ መልኩ አስረድተዋል፤ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 13 ያለ የልብስ መሸጫ ሱቅ ግራቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተዘጋ መሆኑ ስለተረጋገጠ በሌለ ሱቅ ወይም ንብረቶቹ ግምት በቨርባል ተቀማጭ ባልሆነበት ሁኔታ በሌለ ንብረት ፍ/ቤቱ ይካፈሉ ብሎ መወሰን አይችልም፤የቤት ቁሳቁሶች ተጠሪ ምስክሮች ከአመልካች ምስክሮች በተሻለ ንብረቶቹ ከትዳር በፊት ስለመፈራታቸው አስረድተዋል በማለት አመልካች ያቀረበትን

አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶ፤ የኤጀሬ ወረዳ ኢሉ አጋ ቀበሌ በኢንቨስትመንት ለአመልካች የተሰጠ ይዞታ በ2014 ዓ.ም እና 2015 ዓ.ም የተሰራ የግብርና ምርት በባለሙያ ተጣርቶ ምርቱ ከተገኘ ምርቱ በገንዘብ ከተተመነ በኃላ አመልካች ያወጡት ወጪ ታስቦ ተሰጥቶ ትርፉን ለፍ/ቤት ምላሽ ላይ እንዲሰጥ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን አቅርበው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡

አመልካች ጥር 2 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ የቀረበ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ በኮኮብ ቁጥር 1 የመኖሪያ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ አባል ሆነው የቤት መስሪያ 72 ካ.ሜ ይዞታ በ1996 ዓ.ም ተረክበው ለማህበሩ የግንባታ ፍቃድ ከተሰጠ ከሁለት ቀን በኃላ ግንቦት 19 ቀን 1999 ዓ.ም ግራቀኙ ትዳር መስርተው አመልካች በሙያቸው ተጠቅመው ተጠሪ ከማህበሩ በወሰደችው ይዞታ ላይ ለጂ+2 የሚሆን መሰረት እና 9 ፉቲንግ የሰሩ እና ተጠሪም በክስ መስማት ቀን ይህንኑ ሳይክዱ የስር ፍ/ቤት በጋብቻ ውስጥ የተፈሩ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል አቤቱታቸውን ውድቅ ማድረጉ ስህተት መሆኑን፤ ክርክር በተነሳበት ጅምር ቤት ውስጥ ከካርታ ውጪ አስፋፍተው በያዙት ይዞታ ላይ የሰሯቸውን ቤቶች እና ሱቆች እያሉ በ72 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ብቻ በማተኮር የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አለመሆኑን፤ በትዳር ውስጥ የተፈራ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-2-99741 አ/አ የሆነ መኪና ለትዳር ጥቅም የተሸጠ ሳይሆን ለማሸሽ ተብሎ ወደ ተጠሪ እህት የዞረ ስለመሆኑ አመልካች በማስረጃ አስረድተው እያለ መኪናው የተሸጠው ለትዳር ጥቅም ነው መባሉ ስህተት መሆኑን፤ የቤት ቁሳቁስም ከጋብቻ በፊት እና በኃላ የተፈራው በአግባቡ ሳይለይ የተሰጠው ውሳኔ አግባብ አለመሆኑን፤ የኤጀሬ ወረዳ ኢሉ አጋ ቀበሌ የሚገኝ የእርሻ መሬት ዘንድሮ ዓመት የተመረተ ምርት ካለ ታስቦ ይከፈል ሲል የሰጠው ውሳኔ ንብረት ክፍፍል ካደረጉ እና የንብረት ድርሻ ከተለየ በኃላ ከስነ ስርዓት ህግ ውጪ የቀድሞ ውሳኔ ጸንቶ ባለበት የተሰጠ ፍርድ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን፤ የከፍተኛ ፍ/ቤቱም ይህንን ማረም ሲገባው በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ትእዛዝ በመሆኑ በትዕዛዝ ላይ ይግባኝ አይባልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰ/መ/ቁ. 239911

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ በኮከብ ቁጥር 1 የህብረት ስራ ማህበር ጅምር ቤት የግንባታ ፈቃድ በወጣ በ2 ቀን ጋብቻ ተደረገ ከተባለ ግንባታው የተደረገው ጋብቻ ውስጥ ስለሚሆን ለተጠሪ ብቻ መባሉ በጋብቻ ውስጥ ስለተፈራ ንብረት ህጉ በትክክል ተተርጉሟል ወይ? የሚለውን ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ የካቲት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት መልስ ይዘትም አከራካሪው ቤትን በተመለከተ የግንባታ ፍቃድ በ17/09/1999 ዓ.ም የተሰጠ መሆኑን የሚገልጽ ከክፍለ ከተማው መሬትና ልማት ጽ/ቤት የቀረበው ማስረጃ ለግራቀኙ ተሰጥቶ አስተያየት እንዲሰጡበት ሲደረግ አመልካች አሁን ባቀረበበት ጉዳይ ላይ አስተያየት ሳያቀርብ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያቀረበው ክርክር በስር ፍ/ቤት ክርክር ያልተደረገበት እና አዲስ ክርክር መሆኑን፤ አከራካሪው ቤት ግንኙነት ከመመስረታቸው በፊት ያፈሩት እና በላዩ ላይ ዘጠኝ ፋቲንግ ያወጡበት የግል ንብረታቸው መሆኑን፤ በስር ፍ/ቤትም የጋራ ነው በማለት ያላመኑ መሆኑን፤ በይዞታው ላይ እንደሚገኙ የተገለጹት ዘጠኝ ፋቲንግ ገና ከመሬት ውስጥ የሚገኙና እንደ ጅምር ቤት ተደርገው የሚወሰዱ አለመሆናቸውን፤ አመልካች ለግንባታው ያደረገውን አስተዋጽዎ ሳያስረዳ የጋራ ሊባል ይገባል በማለት ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፤ በወቅቱም ማህበሩ ካርታ ያለው መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የግንባታ ፈቃድ ሳይወጣ ግንባታ ይደረግ የነበረ በመሆኑ ተጠሪ ያለፍቃድ ግንባታውን አከናውኛለው የሚል ነው፡፡አመልካች የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የተፈሩ ንብረቶች በመሆናቸው ክፍፍል እንዲደረግባቸው የጠየቋቸው ተጠሪ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ በኮከብ ቁጥር 1 የመኖሪያ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ አባል ሆነው የቤት መስሪያ 72 ካ.ሜ ይዞታ በ1996 ዓ.ም ተረክበው ለማህበሩ የግንባታ ፍቃድ ከተሰጠ ከሁለት ቀን በኋላ ግንቦት 19 ቀን 1999 ዓ.ም ትዳር የመሰረቱ በመሆኑ የተሰሩት 9 ፋቲንግ በጋብቻ ውስጥ ነው፤በጋብቻ ውስጥ የተፈራና የተሸጠው የሰሌዳ

ቁጥር ኮድ-2-99741 አ.አ የሆነ መኪና ለትዳር ጥቅም የተሸጠ አይደለም፣የቤት ቁሳቁስም ከጋብቻ በፊት እና በኃላ የተፈራው በአግባቡ ሳይለይ የተሰጠው ውሰኔ ነው በሚል የቀረበን የሚመለከት ሲሆን በጋብቻ ወቅት የተፈራ ስለመሆኑ ተረጋግጧል ስለሚባልበት እና በጋብቻ ውስጥ የተደረገ ወጪ ለጋብቻ ጥቅም እንደዋለ የሚቆጠርበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

በመሰረቱ በፌዴራሉ የተሻሻለ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 57 እንደተመለከተው ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኂላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ ያመለክታል፡፡ በዚህ መልኩ የተገኙ ንብረቶች የግል ሆነው እንዲቀሩ የተለየ ስምምነት እንዲደረግ ህጉ አያስገድድም፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ግንቦት 19 ቀን 1999 ዓ.ም በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ በኮኮብ ቁጥር 1 የመኖሪያ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ አባል ሆነው የቤት መስሪያ 72 ካ.ሜ ይዞታ በ1996 ዓ.ም ተረክበው ለማህበሩ የግንባታ ፍቃድ የተሰጠው ከጋብቻ በፊት ስለመሆኑ አላከራከረም ፡፡ አመልካች አቤቱታ መሰረቱ የግንባታ ፈቃድ ለማህበሩ ከተሰጠ ከሁለት ቀን በሃላ ጋብቻ የፈጸመን በመሆኑ በይዞታው ላይ የተሰሩት 9 ፉቲንጎች በጋብቻ ውስጥ መሆኑን የሚያሳ በመሆኑ የጋራ ሀብት ነው የሚል ሲሆን በሰር ፍርድ ቤቶች በቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠው ደግሞ እነዚህ ፉቲንጎች ከጋብቻ በፊት ተሰሩ ስለመሆናቸው ነው፡፡ አመልካች በዚህ ይዞታ ላይ ከዚህ ውጭ የተደረገ ተጨማሪ ግንባታ ወይም ማሻሻያ ስለመኖሩ ያቀረቡት መከራከሪያ የለም ፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ በኮኮብ ቁጥር 1 የመኖሪያ ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ ተጠሪ አባል በመሆን የቤት መስሪያ 72 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የተሰሩት 9 ፉቱንጎች የተጠሪ የግል ሀብት ናቸው ሲሉ የሰጡት ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሌላው በአመልካች የተነሳው በጋብቻ ውስጥ የተፈራና የተሸጠው የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-2-99741 አ.አ የሆነ መኪና የተሸጠና ለትዳር ጥቅም አልዋለም በማለት የሚቀርበው እና የቤት ቁሳቁስም የሚመለከት ነው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው የመኪናው ሽያጭ የተከናወነው በትዳር ውስጥ ሲሆን አከራካሪው የሽያጩ ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ውሏል አልዋለም የሚለው ነው፡፡ አንደኛው ተጋቢ በትዳር ውስጥ እያለ በግል ወይም በጋራ ጥረት የተፈራ ንብረት ወይም ገንዘብ ለትዳር ጥቅም ውሏል ወይስ አልዋለም የሚል ክርክር ከተነሳ በተለይም ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም ውሏል በሚባልበት ጊዜ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ለትዳር ጥቅም አልዋለም የሚለው ተከራካሪ ስለመሆኑ

**የሰ/መ/ቁ. 239911**

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 27697 የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በዚህ መሰረትም ገንዘቡ ለትዳር ጥቅም አለመዋሉን አስረድቻለሁ ወይም ማስረጃ ቆጥሬ ታልፎብኛል በሚል አመልካቿ በሰበር አቤቱታቸው የገለጹት ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ከተሽከርካሪው ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ አሁንም ድረስ በተጠሪ ወይም በሌላ በታወቀ ቦታ ይገኛል በሚል የቀረበ ክርክር የለም፡ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሕጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር ስህተት የተፈጸመበት ሁኖ አልተገኘም፡፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የቤት ቁሳቁችን በተመለከት ያነሱት አቤቱታም የስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመዘን የደረሱበት ድምዳሜ ከማስረጃ አቀባበል ሆነ ምዘና አንጻር ስህተት ስለመፈጸሙ አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

በአጠቃላይ አቤቱታ የቀረበበት የውሳኔ ክፍል መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 299723 በጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 202286 ሕዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም በማጽናት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ጸንቷል ፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

## <u>ትእዛዝ</u>

በዚህ መዝገብ ግንቦት 16 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል</u>፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

የሰ/መ/ቁ. 239911